አማርኛ

# የቤት ሰራተኞች ሕግና መመሪያ

ONE ROOF

በቤት ሰራተኞች እና በአሰሪዎች  መብቶች ዙሪያ

የኩዌት ብሔራዊ የማንቃት ዘመቻ

አዘጋጅ

ሶሻል ወርክ ሶሳይቲ

جمعية العمل الاجتماعي

SOCIAL WORK SOCIETY

ሂዩማን ላይን ድርጅት

HUMAN LINE ORGANIZATION

ከኩዌት ፖሊስ ጋር በመተባበር

## ማውጬ


| | |
|---|---|
| ገንዘብ ነክ ጉዳዮች | 4 |
| የአኗኗር ሁኔታዎች | 8 |
| የሥራ ቦታ እና ባህሪያት | 12 |
| የሥራ ሰዓታት እና በዓላት | 16 |
| አጠቃላይ የስራ መብቶች | 18 |
| የቤት ሰራተኞች ኃላፊነቶች | 20 |
| አጠቃላይ መብቶች | 21 |
| ጠለፋ እና የሐሰት እስር | 22 |
| ጥቃት | 26 |
| ጾታዊ ጥቃት | 28 |
| በነዋሪነት ሕግ ዙሪያ ምክር | 32 |
| ሕጋዊ ምክር | 33 |
| ሕጋዊ ሂደቶች | 34 |
| የተጠርጣሪ ዋስትናዎች | 35 |
| ከአገር ማስወጣት እና ከአሰሪ መሸሽ | 36 |
| እስር ቤት በቀጠሮ ማቆየት | 37 |
| የወንጀል ቅሬታ | 38 |
| የስራ ቅሬታ | 40 |
| መጠለያ | 41 |
| የነዋሪነት (ህግ) አይነቶች | 42 |
| ተፈላጊ ቁጥሮችና ቦታዎች | 43 |
| ኩዌት የሚገኙ ኤምባሲዎችና ቆንስላዎች | 44 |
| ከኩዌት ውጭ ያሉ ኤምባሲዎችና ቆንስላዎች | 48 |
| የምርመራ ክፍሎች | 50 |
| ዐቃቤያን ሕግ | 51 |
| የፖሊስ ጣቢያዎች | 52 |
| የኤሌክትሮኒክ አገልግሎቶች | 62 |
| ሕጎች | 63 |

## ስለ አንድ ጣሪያ ዘመቻ

“አንድ ጣሪያ” በቤት ሰራተኞች መብቶች ዙሪያ ግንዛቤን ለማስጨበጥ የሚደረግ ዘመቻ ነው። ዘመቻው በሶሻል ወርክ ሶሳይቲና እና በ ሂውማን ላይን ድርጅት የሚሰራ ሲሆን፣ በአገር ውስጥ ጉዳይሚኒስቴር እንዲሁም ከሌሎች ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ድጋፍ ይደረግለታል።

”አንድ ጣሪያ” ዘመቻ በቤት ሰራተኛ እና አሠሪው መካከል ያለውን ግንኙነት አዎንታዊ ለማደረግ ፤ ብሎም ግንኙነቱ በፍትሃዊነት የሚገዛ በማድረግ የሁለቱንም ወገኖች ክብር እና መብቶችን ለመጠበቅ ያለመነው ። ዘመቻው በኩዌት ሕግ ለቤት ሰራተኞች የተሰጡ መብቶች ላይ ግንዛቤ በማስጨበጥ የቤት ሠራተኞችን በተመለከተ የወጡ ህጎችን ካለመረዳት የተነሳ የቤት ሰራተኞች ሊገጥሟቸው የሚችሉ ችግሮችን ወይም አለመግባባቶችን ለመቀነስ ያለመም ነው።

”አንድ ጣሪያ” ዘመቻ የቤት ሰራተኝነት በሕግና ሥርዓት መመራት የሚገባው ሥራ መሆኑን በአጽዕኖት ይገልጻል።

## ስለ ሕግና መመሪያው

ኩዌት ውስጥ በአሰሪው እና የቤት ሰራተኛው መካከል ያለው ግንኙነት በብዙ ጉዳዮች ላይ አመርቂ እና ስኬታማ ቢሆንም ፣ ሥራዎቻቸውን የሚመለከቱ ሕጎችን በማወቅ መብቶቻቸው በሚጣሱ ጊዜ የመብት ይገባኛል ጥያቄ ለማቅረብ የቤት ሰራተኞች ያላቸውን መብቶችና ግዴታዎች ማወቅ አስፈላጊ ነው።

ይህ ህግና መመሪያ በቀላልንገድ የተገለጹና ተአማኒነት ያላቸው ፡-

- የቤት ውስጥ ሥራን በሚመለከት የወጡ ሕጎችን፣ ደንቦችን፣ እንዲሁም እነዚህን ሕጎች የሚመለከቱ መመሪያዎችን በተመለከተ፣
- መኖሪያ ፈቃድ ህጎችን በተመለከተ፣
- የወንጀለኛ መቅጫ ሕጎችን በተመከለተ፣
- ማንኛውም ሰው ቅሬታ የሚያቀርብባቸውን፣ ክስተቶችን የጠቁምባቸውን እና ዕርዳታ የሚጠይቅባቸውን ቦታዎች በተመለከተ
- ጠቃሚ የሆኑ የቃላት ትርጓሜዎችን በተመለከተ መረጃ ይሰጣል።

| አርእስት | መብት | አንቀፅ |
| --- | --- | --- |
| የጸመወዝ ክፍያና ስለሚቆረጥበት ሁኔታ | • የሚከፈለው ጸመወዝ በውሉ ውስጥ ከተጠቀሰው የጸመወዝ መጠን ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት።<br>• ጸመወዙ በየወሩ መጨረሻ ይከፈላል።<br>• ጸመወዙ የሚሰላው ሥራ ከተጀመረበት ቀን ጀምሮ ነው።<br>• ጸመወዝ መቀነስ አይፈቀድም። | • አንቀጽ 7 - 8 የቤት ሰራተኞች ህግ |
| ተጨማሪ ስራ | • ከስራ ሰዓት ወይም ቀን ውጭ ለሥራ የተመደበ ሲሆን ሰራተኛው ለተጨማሪ ስራው ከተመሳሳይ ወቅት ነባር ክፍያ እጥፍ ያላነሰ ገንዘብ የማግኘት መብት አለው። | • አንቀጽ 28 የቤት ሰራተኞች ህግ |

| ቅጣት | የማመለከቻ ቦታ | ማስረጃ |
| --- | --- | --- |
| • ሰራተኛው ጸመወዙ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ወራት 10 ዲናር ካሳ ይከፈለዋል | • ለቤት ሰራተኞች ቅጥር ክፍል | • ከተግባራዊ የስራ አገልግሎት ዘመን ጋር የተጣጣመ የደሞዝ መቀበያ ወይም የሀዋላ ደረሰኝ አለመኖር |
| • ለሰራተኛው ተጨማሪ ማካካሻ ክፍያ መስጠት። | • ለቤት ሰራተኞች ቅጥር ክፍል | • ክስተቱን ማመልከት<br>• ምስክር |

| አርእስት | መብት | አንቀፅ |
|---|---|---|
| የአገልግሎት የስንብት ክፍያ | • ውሉ ሲያልቅ ሰራተኛው የሚገባውን መብት በሙሉ ማግኘት ይችላል።<br>• ሰራተኛው/ዋ የአገልግሎትበ ስንብት ክፍያ የሚያገኘው/ የምታገኘው የኮንትራት ውሉን ጊዜ ከጨረሰ/ች ነው።<br>• የአገልግሎት የክፍያው የገንዘብ መጠን የሚሰላው ለእያንዳንዱ አመታት የ1 ወር ደሞዝ በሚሆን ግምት ነው። | • አንቀፅ 11የውስጥ ደንቦች<br>• አንቀፅ 15 የውስጥ ደንቦች<br>• አንቀፅ 23 የቤት ሰራተኛ ሕግ |
| የምልመላ ቢሮ ከሰራተኛው ገንዘብ ስለመሰብሰብ | • በኩዌት ውስጥም ሆነ ከኩዌት ውጭ ሰራተኞችን የሚመለምለው የሰራተኛ አቅራቢ ቢሮ በቀጥታም ሆነ በሌሎች ተቀጣሪዎች በኩል ወይም በሌሎች ግንኙነት ካላቸው መሰል ተቋማት ምንም አይነት ገንዘብ ከቤት ሰራተኛ መቀበል አይፈቀድለትም። | • አንቀፅ 4 የቤት ሰራተኛ ሕግ |

| ቅጣት | የማመለከቻ ቦታ | ማስረጃ |
|---|---|---|
| • ተገቢውን ዋጋ መክፈል<br>• ለቀጣሪው የሚሰጠውን የመግቢያ ቪዛ የመስጠት ተግባር ለ6 ወራት ማገድ | • ለቤት ሰራተኞች ቅጥር ክፍል | • የአገልግሎት የስንብት ክፍያ የባንክ ወይም የሀዋላ ደረሰኝ አለመኖር |
| • ፈቃዱን ማገድ<br>• በማጭበርበር ፣ በህገ ወጥ መንገድ ሀብት በማካበት ወንጀል መክሰስ | • የቤት ሰራተኞች አስተዳደር<br>• የአካባቢው ፖሊስ ጣቢያ | • ማንኛወም ማስረጃ (እንደ የባንክ ደረሰኝ/ የሰው ምስክር) ያሉት |

| አርእስት | መብት | አንቀፅ |
| --- | --- | --- |
| መኖርያ/መጠከያ | • አሰሪው ከሰራተኛው በቂ ማረፊያ፣ እንዲሁም ንጹህና ጤናማ የኑሮ ሁኔታ እንዲኖረው ማድረግ ይኖርበታል። | • አንቀፅ 11 የቤት ሰራተኛ ሕግ<br>• አንቀፅ 8(7) የአስተዳደር ደንቦች |
| ልብስ | • አሰሪው ከቤት ሰራተኛው በቂና ምቹ ልብስ ማቅረብ ይኖርበታል። | • አንቀፅ 9 የቤት ውስጥ ሰራተኛ ሕግ<br>• አንቀፅ 8(5) የአስተዳደር ደንቦች |

| ቅጣት | የማመለከቻ ቦታ | ማስረጃ |
| --- | --- | --- |
| • ከቀጣሪው የሚሰጠውን የመግቢያ ቪዛ የመስጠት ተግባር ከ6 ወራት ማገድ | • ከቤት ሰራተኞች ቅጥር ክፍል | • ክስ<br>• ምስክሮች |
| • ከቀጣሪው የሚሰጠውን የመግቢያ ቪዛ የመስጠት ተግባር ከ6 ወራት ማገድ | • ከቤት ሰራተኞች ቅጥር ክፍል | • ክስ<br>• ምስክሮች |

| አርእስት | መብት | አንቀፅ |
| --- | --- | --- |
| የሰራተኛ ጤንነት | • የስራው ባለቤት የቤት ሰራተኛውን ማሳከም ያለበት ሲሆን ህክምናውም በመንግስት ሆስፒታሎች መደረግ ይኖርበታል። | • አንቀፅ 9 የቤት ሰራተኛ ሕግ<br>• አንቀፅ 8(6) የአስተዳደር ደንቦች |
| ሰራተኛን በቢሮ ማኖር | • የሰራተኛ አቅራቢ ቢሮውን በምንም አይነት ሁኔት የሰራተኛ ማደርያ ማድረግ አይፈቀድም፣ ከቢሬ የተከየ ማረፊያ ማዘጋጀት ይኖርበታል። | • አንቀፅ 4 የቤት ሰራተኛ ሕግ<br>• አንቀፅ 49 የቤት ሰራተኛ ሕግ<br>• አንቀፅ (6) 8 የአስተዳደር ደንቦች |

| ቅጣት | የማመልከቻ ቦታ | ማስረጃ |
| --- | --- | --- |
| • ከቀጣሪው የሚሰጠውን የመግቢያ ቪዛ የመስጠት ተግባር ከ6 ወራት ማገድ | • ከቤት ሰራተኞች ቅጥር ክፍል | • ክስ<br>• ምስክሮች |
| • ፈቃዱን መሰረዝ | • ከቤት ሰራተኞች ቅጥር ክፍል | • ክስተቱን ማመልከት |

| አርእስት | መብት | አንቀፅ |
|---|---|---|
| የስራ መዘርዝር | • አሰሪው ሠራተኛው እንዲሰራ የሚያዝዝ መብት ያለበው በኮንትራት ውሉ ውስጥ የተገለጹትን ተግባራት ብቻ ነው። | • አንቀፅ 18 የቤት ሰራተኛ ሕግ<br>• አንቀፅ 14 - የቤት ሰራተኛ ሕግ<br>• አንቀፅ 9 (2) የአስተዳደር ደንቦች |
| የሥራ ቦታን መለየት | • የሠራተኛው የሥራ ቦታ በስራ ውል ውስጥ ይወሰናል። አሠሪውም ሌላ ቦታ እንዲሰራ እንዲመድበው አይፈቅድለትም። | • አንቀፅ 18 የቤት ሰራተኛ ሕግ<br>• አንቀፅ 14 - የቤት ሰራተኛ ሕግ |

| ቅጣት | የማመልከቻ ቦታ | ማስረጃ |
|---|---|---|
| • ከቀጣሪው የሚሰጠውን የመግቢያ ቪዛ የመስጠት ተግባር ከ6 ወራት ማገድ | • ከቤት ሰራተኞች ቅጥር ክፍል | • ክስ<br>• ምስክሮች |
| • ከቀጣሪው የሚሰጠውን የመግቢያ ቪዛ የመስጠት ተግባር ከ6 ወራት ማገድ | • ከቤት ሰራተኞች ቅጥር ክፍል | • ክስ<br>• ምስክሮች |

| አርእስት | መብት | አንቀፅ |
|---|---|---|
| አጸገኛ እና ክብረ - ነክ የሆኑ ሥራዎች | • አሠሪው ሠራተኛውን የሚጎዳ ወይም ለጤንነቱ አስጊ የሆነ እንዲሁም ሰብዓዊ ክብርን አደጋ ላይ በሚጥል ሥራ ማሰራት አይችልም። | • አንቀጽ 10 የቤት ሰራተኛ ሕግ |
| ለሌላ ወገን መስራት | • አሠሪው የቤት ሰራተኛውን ለሌላ ሰው የማሰራት መብት የለውም። | • አንቀጽ 8 የአስተዳደር ደንቦች |
| ከኩዌት ውጭ መስራት | • አሠሪው ያለ ሰራተኛው ፈቃድ ወደ ሌላ ሀገር ሰራተኛውን ወስዶ የማሰራት መብት የለውም። | • አንቀፅ 46 የቤት ሰራተኛ ሕግ<br>• አንቀፅ 8 (10) የአስተዳደር ደንቦች |

| ቅጣት | የማመልከቻ ቦታ | ማስረጃ |
|---|---|---|
| • ከቀጣሪው የሚሰጠውን የመግቢያ ቪዛ የመስጠት ተግባር ከ6 ወራት ማገድ | • ከቤት ሰራተኞች ቁጥር ክፍል | • ምስክሮች<br>• ማንኛውም የጤና ችግር ካለ የህክምና የምስክር ወረቀት |
| • አሠሪው በራሱ ወጪ ሠራተኛውን/ዋን ወደ ሀገሩ/ሯ ይመልሳል | • ከቤት ሰራተኞች ቁጥር ክፍል | • ክስተቱን ማመልከት |
| • አሠሪው በራሱ ወጪ ሠራተኛውን/ዋን ወደ ሀገሩ/ሯ ይመልሳል | • ከቤት ሰራተኞች ቁጥር ክፍል | • ክስተቱን ማመልከት |

| አርእስት | መብት | አንቀፅ |
|---|---|---|
| ከፍተኛው 12 የስራ ሰዓታት | • የቤት ሰራተኞች ከፍተኛ የስራ ሰዓታት ከእረፍት ጋር በቀን 12 ሰዓታት ነው። | • አንቀጽ 22 (3) የቤት ሰራተኞች ሕግ<br>• አንቀጽ 12 (2) የአስተዳደር ደንቦች |
| ዓመታዊ እና ሳምንታዊ እረፍት | • የቤት ሰራተኛው ቢያንስ በሳምንት የአንድ ቀን እና ከጸመወዝ ጋር የዓመት ዕረፍት የማግኘት መብት አለው። | • አንቀጽ 22 (3) የቤት ሰራተኞች ሕግ<br>• አንቀጽ 12 (3) የአስተዳደር ደንቦች |

| ቅጣት | የማመለከቻ ቦታ | ማስረጃ |
|---|---|---|
| • ከቀጣሪው የሚሰጠውን የመግቢያ ቪዛ የመስጠት ተግባር ከ6 ወራት ማገድ<br>• የስራ ቀናት እና ሰዓታትን አንደ ተጨማሪ ስራ መቁጠር | • ከቤት ሰራተኞች ቅጥር ክፍል | • ምስክሮች<br>• የትርፍ ሰዓት ስራ ደረሰኝ አለመኖር<br>• ክስ |
| • ከቀጣሪው የሚሰጠውን የመግቢያ ቪዛ የመስጠት ተግባር ከ6 ወራት ማገድ<br>• የስራ ቀናት እና ሰዓታትን አንደ ተጨማሪ ስራ መቁጠር | • ከቤት ሰራተኞች ቅጥር ክፍል | • ክስ<br>• ምስክሮች |

| አርእስት | መብት | አንቀፅ |
| --- | --- | --- |
| አደጋ ከደረሰበት/ባት ሰራተኛ ህክምና እና ካሣ ስለ መስጠት | • የቤት ሰራተኛው/ዋ በሥራ ላይ እያለ/ች ወይም በስራ ሰዓት ውስጥ አደጋ ቢደርስበት/ባት ቀጣሪው የማሳከም እና የጉዳት ካሳ የመክፈል ግዴታ አለበት። | • አንቀጽ 22 (1) የቤት ሰራተኞች ሕግ<br>• አንቀጽ 13 (3) የአስተዳደር ደንቦች |
| የግል ሰነዶች እና የማንነት ማረጋገጫዎችን ስለመያዝ | • አሠሪው ያለ ሰራተኛው/ዋ ፈቃድ የሰራተኛውን ፓስፖርት ወይም ሌሎች የግል ሰነዶችን መያዝ የለበትም። | • አንቀፅ 12 የቤት ሰራተኞች ሕግ<br>• አንቀፅ 22 (4) የቤት ሰራተኞች ሕግ<br>• አንቀፅ 8 (8) የአስተዳደር ደንቦች |
| የሰራተኛን አስከሬን ስለማጓጓዝ | • ሰራተኛው ሞት ባጋጠመው ጊዜ አሠሪው አስከሬኑን ወደ አገሩ የማጓጓዝ ሃላፊነት ያለበት ሲሆን፣ የሞተበትን/ችበትን ወር የደመወዝ ክፍያ መፈፀም አለበት። | • አንቀጽ 22 (5) የአስተዳደር ደንቦች |

| ቅጣት | የማመልከቻ ቦታ | ማስረጃ |
| --- | --- | --- |
| • በስራ ላይ ለደረሰ ጉዳት ለቤት ሰራተኛው ካሳ መክፈል | • ክስተቱ ለተከሰበት ለአካባቢው ፖሊስ ጣቢያ<br>• የቤት ሰራተኞች ቅጥር ክፍል | • የሕክምና ማስረጃ<br>• ክስተቱን ማመልከት |
| • ሰነዶችን ለሰራተኛው መስጠት<br>• በጊዜያዊነት ለቀጣሪው የሚሰጠውን የመግቢያ ቪዛ የመስጠት ተግባር ከ6 ወራት ማገድ | • የቤት ሰራተኞች ቅጥር ክፍል | • ክስ<br>• ምስክሮች |
| • ለቀጣሪው የሚሰጠውን የመግቢያ ቪዛ የመስጠት ተግባር ከ6 ወራት ማገድ | • የቤት ሰራተኞች ቅጥር ክፍል | • የሞት ምስክር ወረቀት ኮፒ |

| አርእስት | ኃላፊነቶች | አንቀጽ |
| --- | --- | --- |
| ትዕዛዞችን መፈጸም | • የቤት ሰራተኛው/ዋ በውሉ ውስጥ በተጠቀሰው መሠረት የአሰሪውን ትእዛዞች መፈጸም አለበት/ባት። | • አንቀፅ 13 የቤት ሰራተኞች ሕግ<br>• አንቀፅ 9 የአስተዳደር ደንቦች |
| የስራ አፈፃፀም | • ሰራተኛው/ዋ በኮንትራት ውሉ ውስጥ የተቀመጡትን ስራዎች ማከናወን እና ለትግበራው ጥንቃቄ ማድረግ አለበት/ባት። | • አንቀፅ 14 የቤት ሰራተኞች ሕግ<br>• አንቀፅ 9 የአስተዳደር ደንቦች |
| ንብረት እና ሚስጥሮችን መጠበቅ | • ሠራተኛው/ዋ የአሠሪውን እና የቤተሰቡን ንብረቶች በአግባቡ መያዝ አለበት/ባት፤<br>• እንዲሁም ምስጢሮች መጠበቅ ይኖርበታል/ባታል። | • አንቀፅ 15 የቤት ሰራተኞች ሕግ<br>• አንቀፅ 9 የአስተዳደር ደንቦች |

**1 —**

የቤት ሰራተኛው/ዋ ኩዌት በደረሰ/በደረሰች በ 24 ሰዓታት ውስጥ ቀጣሪው ሊቀበለው/ሊቀበላት ይገባል

**2 —**

ለአሰሪና ሠራተኛ ችሎት የክስ አቤቱታ ማስገባት ካስፈለገ ለዳኝነት የሚከፈል ክፍያ የለም

**3 —**

ሰራተኛው/ዋ በአሠሪው ላይ ቅሬታ ካሰማና አሰሪው መኖሪያ ፈቃዱን ካሰረዘው፣ ቅሬታው እስኪፈታ ድረስ ለጊዜያዊ ቆይታ የመኖርያ ፈቃድ ማመልከት ይችላል

**4 —**

የቤት ሰራተኛው የሥራ ቅጥር የውል ስምምነቱን የመያዝ መብት አለው። የኮንትራት ውሉ የተጻፈው በተለያዩ ቋንቋዎች በሚሆንበት ጊዜና የኮንትራት ውል ስምምነቱ በአተረጓጎም ላይ ክርክር የሚያስነሳ በሚሆንበት ጊዜ የአረብኛው ጽሑፍ የበላይነት ይኖረዋል

| አርእስት | ትርጉም | አንቀጽ |
|---|---|---|
| የሐሰት እስር | • የሐሰት እስር ማለት አንድን ግለሰብ ከፈቃዱ ውጭ በሕግ ባልተገደበ ሁኔታ ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ እንዳይንቀሳቀስ መከልከል ነው። | • የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀፅ 184 |
| ከአካላዊ ማሰቃየት የሚደረግ እስር | • ከአካላዊ ማሰቃየት እና የሞት ዛቻና ማስፈራሪያ ጋር የተዛመደ ነው። | • የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀፅ 184 |

| ቅጣት | የማመልከቻ ቦታ | ማስረጃ |
| --- | --- | --- |
| • ይህንን ህግ የተላለፈ ከ 3 ዓመት በማይበልጥ አሥራት ወይም በ 3 ሺህ የኩዌት ዲናር ወይም በሁለቱም መቀጮ ይቀጣል | • በአደጋ ጊዜ ስልክ ቁጥር መደወል (የመጀመሪያ ሪፖርት)<br>• ክስተቱ ለተከሰተበት የአካባቢው ፖሊስ ጣቢያ | • የአደጋ ጊዜ ጥሪ ቁጥሮች ጋር የተደረገ ግንኙነት<br>• ምስክሮች |
| • ይህ ከባድ ወንጀል ከ 7 ዓመት በማይበልጥ አሥራት ወይም ከ 7 ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ ቅጣት የይቀጣል | • በአደጋ ጊዜ ስልክ ቁጥር መደወል (የመጀመሪያ ሪፖርት)<br>• ክስተቱ ለተከሰተበት የአካባቢው ፖሊስ ጣቢያ | • ክስተቱን በፍጥነት ሪፖርት ማድረግ<br>• ሁሉንም ማስረጃዎች ማስቀመጥ (ለምሳሌ አይታጠቡ ወይም ልብሶችዎን አይጠቡ)<br>• የሆስፒታል ሪፖርት<br>• ምስክሮች |

| አርእስት | ትርጉም | አንቀጽ |
|---|---|---|
| የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ከመፈጸም በማሰብ ክብርን የሚያጎድፍ ጥቃት መፈጸምና ማገት | • ለመጉዳት፣ ጾታዊ ወይም ክብርን በሚያጎድፍ መልኩ ጥቃት ለማድረስ፣ ለዝሙት አዳሪነት ለማስገደድ፣ ለማጭበርበር ወይም ለመግደል በማሰብ አንድን 21 ዓመት የሞላውን ጤነኛ ሰው ማገት ማለት ነው። | • የወንጀለኛ መቅጫ ህግአንቀፅ 180 |
| አግቶ ስለማቆየት | • አድሜው ከ 21 አመት በታች የሆነን የአእምሮ ውስንነት ወይም ህመም ያለበትን ሰው ያለራሱ ፈቃድ ከሚኖሩበት ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በመወሰድ ያለ ፈቃዱ መገት ነው። | • የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀፅ 178<br>• የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀፅ 179 |

| ቅጣት | የማመልከቻ ቦታ | ማስረጃ |
|---|---|---|
| • በሞት የሚያስቀጣ ከባድ ወንጀል ነው | • በአደጋ ጊዜ ስልክ ቁጥር መደወል (የመጀመሪያ ሪፖርት)<br>• ክስተቱ ከተከሰተበት የአካባቢው ፖሊስ ጣቢያ | • ክስተቱን በፍጥነት ሪፖርት ማድረግ<br>• ሁሉንም ማስረጃዎች ማስቀመጥ (ከምሳሌ አይታጠቡ ወይም ልብሶችዎን አይጠቡ)<br>• የሆስፒታል ሪፖርት<br>• ምስክሮች |
| • ይህ ከባድ ወንጀል እንደየሁኔታው ይወሰናል፤ ከ3 - 15 ዓመት ሊደርስ በሚችል የእስር ቅጣት ሊቀጣ ይችላል | • በአደጋ ጊዜ ስልክ ቁጥር መደወል (የመጀመሪያ ሪፖርት)<br>• ክስተቱ ከተከሰተበት የአካባቢው ፖሊስ ጣቢያ | • የክስተቱ ሪፖርት<br>• የሀኪም ማስረጃ<br>• ምስክሮች |

| አርእስት | ትርጉም | አንቀጽ |
|---|---|---|
| ቀላል ጥቃት | • ቀላል ጥቃት ሲሆን መትፋትን፣ ፀጉርን ወይም ልብስ መጎተትን፣ ወይም በውሃ መርጨትን፣ እንዲሁም ምልክት ያላሳረፈ አካላዊ ድብደባን ያጠቃልላል። | • የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀጽ 163 |
| መጠነኛ አካላዊ ጉዳት | • ቀላል ድብደባ ሲሆን በሰውነት ላይ ምልክት የሚተው እና መቁሰልን የሚያስከትልን ድብደባ ያጠቃልላል። | • አንቀጽ 160 የወንጀለኛ መቅጫ ህግ |
| ከባድ ድብደባ | • ከባድ ድብደባ ሲሆን እንደ ቢላዋ፣የጦር መሳሪያ፣ቃጠሎ የሚያስከትሉ አደገኛ ቁሳቁሶችን ወ.ዘ.ተ በመጠቀም የሚፈጸምና እና ቋሚ የአካል ጉዳትን የሚያስከትል ድብደባን ይጨምራል። | • የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀጽ 161<br>• የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀጽ 162 |

| ቅጣት | የማመልከቻ ቦታ | ማስረጃ |
| --- | --- | --- |
| • ይህንን ህግ የተላለፈ ከ 3 ወራት በማይበልጥ እሥራት ወይም በ 3 መቶ የኩዌት ዲናር ወይም በሁለቱም መቀጮ ይቀጣል | • ክስተቱ ከተከሰተበት ከአካባቢው ፖሊስ ጣቢያ | • ምስክሮች |
| • ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እስራት እና ከ 2ሺህ ዲናር የማይበልጥ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል | • ክስተቱ ከተከሰተበት ከአካባቢው ፖሊስ ጣቢያ | • የምስክሮች ቃልና<br>• ወደ ፎረንሲክ ምርመራ ሪፈር ከተጠየቀበት ጋር ከአካባቢያው ሆስፒታል የተሰጠ የሀኪም ማስረጃ ( ሆኖም ህክምናው ሪፈር የሚያስፈልገው ሆኖ ሳለ መርማሪው ወደ ፎረንሲክ ምርመራ ባለሙያ የመሄድ ጥያቄውን ካልተቀበለውና በቃል መቀበያ ማህደር ላይ ጥያቄ መቅረቡ እስካልተጠቀሰ ድረስ ፊርማ ማህደር ውስጥ ማኖር አይገባም) |
| • ከ 10 ዓመት በማይበልጥ እስራት እና በተጨማሪም ለመንግስት ገቢ የሚሆን ከ10ሺህ ዲናር ገንዘብ ቅጣት ሊጨምር ይችላል | • ክስተቱ ከተከሰተበት ከአካባቢው ፖሊስ ጣቢያ | |

| አርእስት | ትርጉም | አንቀጽ |
|---|---|---|
| ነውር ተግባር በስውር መስራት | • አንድ ሰው ያለ ሴቷ ፈቃድ በድብቅ የሴትን ክብር የሚያነውርና አሳፋሪ ድርጊት ከፈፀመ ፤ | • የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀፅ 199 |
| ክብርን ማጉደፍ | • አንድን ከ21 ዓመት ወይም ከዚህ በላይ ዕድሜ ያለውን ሰው ያለ ፈቃዱ አካሉን መነካካት ወይም ልብሱን ማውለቅ፤ ወይም ከ21 ዕድሜ በታች የሆነን ሌላ ሰው ያለ ፈቃዱ ማንኛውንም አይነት ንክኪ ካደረገ ወይም ልብሱን ማውለቅ። | • የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀፅ 191 ህግ |

| ቅጣት | የማመልከቻ ቦታ | ማስረጃ |
|---|---|---|
| • ይህንን ህግ የተላለፈ ከ 1 ዓመት በማይበልጥ እሥራት ወይም በ 1 ሺህ የኩዌት ዲናር በማይበልጥ ገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል | • በአደጋ ጊዜ ስልክ ቁጥር መደወል<br>• ክስተቱ ከተከሰተበት ከአካባቢው ፖሊስ ጣቢያ | • ክስተቱን ማመልከት<br>• ምስክሮች |
| • ይህንን ህግ የተላለፈ ተጠቂው/ዋ የቤት ሰራተኛው/ዋ ከሆነ/ች አጥፊው/ዋ አድሜ ልክ እስራት ይቀጣል | • በአደጋ ጊዜ ስልክ ቁጥር መደወል<br>• ክስተቱ ከተከሰተበት ከአካባቢው ፖሊስ ጣቢያ | • ክስተቱን ማመልከት<br>• የምስክሮች<br>• የህክምና ሪፖርት |

| አርእስት | ትርጉም | አንቀጽ |
| --- | --- | --- |
| በማስገደድ፣ በማስፈራራት፣ ወይም በማታለል ግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም | • ብልትን በማስገባት ፍቃድ ሳይኖር በማስፈራራት፣ በማስገደድና በማታለል ጾታዊ ግንኙነት ማድረግ። | • የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀፅ 186 |
| ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር | • የግዳጅ ሥራ ለማሰራት ወይም የወሲብ ተግባርን ለመፈፀም በአንድ ወይም በብዙ ሰዎች የሌላውን ሰው ነጻነት መከልከል ወይም ደግሞ ከ ፈቃዱ/ዷ ውጭ ሥልጣንን በመጠቀም፣ በጉልበት ወይም በማታለል ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ማዘዋወር። | • ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ህግ አንቀፅ 1<br>• ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር አንቀፅ 2 |

| ቅጣት | የማመልከቻ ቦታ | ማስረጃ |
| --- | --- | --- |
| • ይህንን ህግ የተላለፈ በሞት ወይም በአድሚ ልክ አስራት ይቀጣል። ተበዳይ በስሩ የሚተዳደር ከሆነና በቤት ሰራተኝነት የምትሰራለት ከሆነ (ወንጀል ፈፃሚው በሞት ይቀጣል። | • በአደጋ ጊዜ ስልክ ቁጥር መደወል<br>• ክስተቱ ከተከሰተበት ከአካባቢው ፖሊስ ጣቢያ | • በአፋጣኝ የቀረበ አቤቱታ<br>• ሁሉንም ማስረጃዎችዎን ማስቀመጥ (ለምሳሌ አይታጠቡ ወይም ልብሶችዎን አይጠቡ)<br>• የህክምና ማስረጃ<br>• ምስክሮች |
| • በ 15 ዓመት እሥራት ይቀጣል። (ሲረጋገጥ በፍላጎት ዝሙት የፈፀመ ቅጣት አይኖርበትም) | • የአደጋ ጊዜ ስልክ ቁጥር<br>• የአካባቢ ፖሊስ ጣቢያ (ተጠቂው ወደ ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀል ምርመራ ክፍል ይተላለፋል) | • ክስተቱን ማሳወቅ<br>• ምስክሮች<br>• የወንጀል ምርመራዎች |

**1 —**

ከ 6 ወር ኩዌት ውስጥ አለመኖር መኖሪያ ፈቃዱ ውድቅ እንዲሆን ያደርገዋል።

**2 —**

ከኩዌት አገር ለመውጣት የሚጠባበቅ አንድ የውጭ ዜጋ ትዕዛዙን ለማስፈጸም እንደ አስፈላጊነቱ ከ30 ቀን ላልበለጠ ጊዜ እስር ቤት ሊቆይ ይችላል።

**3 —**

የመኖያ ፈቃድ የሌለው ወይም  የፈቃዱ ጊዜው ያለፈበት አንድ የውጭ  ዜጋ በአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር ትዕዛዝ ከኩዌት እንዲወጣ ሊደረግ ይችላል።   ይህ የውጭ ዜጋ አስፈላጊ ሁኔታዎች ከተሟሉ ወደ ኩዌት ሊመለስ ይችላል።

**4 —**

በኩዌት ውስጥ በሕገ ወጥ መንገድ የሚኖር ማንኛውንም የውጭ ዜጋ  ከለላ መስጠት፣ ማኖርና ማሰራት የተከለከለ ነው። በተጨማሪም ለሶሰተኛ ወገን አሳልፎ ማሰራት ክልክል ነው።

**5 —**

ከኩዌት እንዲወጣ የተደረገ የውጭ  ዜጋ  በአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር  ልዩ ፈቃድ ካልተሰጠው በስተቀር ወደ አገሪቱ ላይመለስ ይችላል።

## 1 —

ውልን ለማቋረጥ የፈለገ ሰራተኛ ለአሰሪው ቢያንስ ውሉ ከመጠናቀቁ በፊት ሁለት ወራት አስቀድሞ ማሰወቅ ይኖርበታል። አለበለዚያ የነበረው ውል እንዲቀጥል እንደተስማሙ ተቆጥሮ ውሉ የሚታደስ ይሆናል።

## 2 —

በሃይማኖቶች እና እምነቶች ላይ ማፌዝ እና ማዋረድ በኩዌይ ሕግ ወንጀል ነው።

## 3 —

በስምምነት ከጋብቻ ውጭ የተፈፀመ የወሲብ ግንኙነት በህግ ያስቀጣል ። ድርጊቱ የተፈጸመው ከ 21 ዓመት በታች ከሆኑ ልጃገረዶች ጋር ከሆነ ወይም ደግሞ ከሁለቱ ወገኖች አንዱ ባለትዳር ከሆኑ ቅጣቱ የከበደ ይሆናል።

## 4 —

ሰዎችን በዝሙት ሥራ ማሰማራት በኩዌት ሕግ ወንጀል ነው።

## 5 —

በስምምነት በወንዶች መካከል መሀከል የሚደረግ የግብረ ሦጋ ግንኙነት በኩዌት ሕግ ወንጀል ነው

## 6 —

ከጋብቻ ውጭ እርግዝና መፈፀም በሕግ የሚያስቀጣ ነው።

## 7 —

ውርጃ በኩዌት ሕግ ወንጀል ነው።

## 8 —

ማንኛውም ሰራተኛ ያለአሰሪው ፈቃድ ወደ ማንንም ሰው ወደ ቤት ውስጥ መግባት የተከለከለ ነው።

| አርእስት | የማመልከቻ ቦታ | ምዝገባ | የውሳኔ ሂደት | ፍርድ ቤት |
|---|---|---|---|---|
| የጾንብ መተላለፍ የአወሳሰን ሂደቶች | አቤቱታዎን ክስተቱ በተከሰተበት አካባቢው ፖሊስ ጣቢያ ያቅርቡ። | ጉዳዮን ከመርማሪው ፖሊስ ስመዝግቡ፣ ከዚያም ለምርመራ ኃላፊው ይቀርባል። | ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት ለማቅረብም ሆነ ለመዝጋት፣ ጉዳዩ ወደ ዐቃቢ ህግ ይቀርባል ( በጠቅላላ ምርመራ ክፍል ሥር ) ። አቤቱታው ውድቅ ከተደረገ አቤት ባዩ ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው። | በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ፣ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እና በሰበር ሰሚ ችሎት ፍርድ ቤቶች ጨምሮ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በበርካታ የፍርዱን ሂደት ያከናውናሉ። |
| የወንጀለኝነት ያወሳሰን ሂደቶች | አቤቱታዎን ለአካባቢው ፖሊስ ጣቢያ ወይም ደግሞ ለዓቃቤ ህግ ቢሮ ያቅርቡ። | ጉዳዩን ለአቃቤ ህግ ማስመዝገብ። | አቃቤ ሕጉ በጉዳዩ ላይ ክስ ሊመሰርት ወይም መዝገቡን ሊዘጋው ይችላል። ሆኖም ክስ ሳይመሰረት መዝገቡ ከተዘጋ ባለጉዳዩ ይግባኝ የማለት መብት አለው። | በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ፣ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እና በሰበር ሰሚችሎት ፍርድ ቤቶች ጨምሮ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በበርካታ የፍርዱን ሂደት ያከናውናሉ። |

## በእስር እና በምርመራ ወቅት  የሚደረግ ጥበቃ

- የፖሊስ አባላት በተጠርጣሪው ላይ  አካላዊ ወይም ስነ ልቦናዊ ጥቃት ማድረስ አይችሉም።
- መርማሪው ተከሳሹ ባቀረበው ጥያቄ መሰረት አንድ ግለሰብ በተያዘበት ወቅት በፖሊስ የደረሰበትን ጉዳት ለማረጋገጥ ወደ ህጋዊ የህክምና ተቋም  መላክ አለበት ።
- መርማሪው ይህንን ለማድረግ ፈቃደኛ ካልሆነ  ተከሳሹ  በሪፖርቱ ላይ ያለመፈረም መብት ይኖረዋል ።
- የምርመራ ሪፖርቱ ለተካሳሹ መነበብ ይኖርበታል።   ሪፖርቱ ለተከሳሹ ሲነበብ ከእርሱ ቃል ጋር የሚቃረን ከሆነ ወይም የተሟላ ካልሆነ ያለመፈረም መብቱ የተጠበቀ ነው።

## በወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘ ግለሰብ ዋስትናዎች

- ለእስሩ መንስኤ የሆኑ ምክንያቶች በጽሑፍ ይገለፅለታል።
- ከምርመራው በፊት ከጠበቃው ጋር የመነጋገር መብት አለው።
- ከጠበቃው ጋር እስከሚገናኝ ድረስ ያለመናገር መብት አለው፤ መርማሪው ጠበቃውን  የማስወገድ መብት የለውም።

## በአስተዳደራዊ ውሳኔ ከአገር ማስወጣት

- የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትር ማንኛውም የውጭ ዜጋን ከአገሪቱ እንዲወጣ ውሳኔ ሊያስተላልፍ ይችላል፤ የውጭ ዜጋው ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት የለውም። ሌላ ውሳኔ ከአገር ውስጥ ሚኒስትር ካልመጣ በስተቀር ውሳኔው አይሻርም።
- የውጭ ዜጎች የመኖሪያ ፈቃድ ህግ አንቀፅ 16
- የውጭ ዜጎች የመኖሪያ ፈቃድ ህግ አንቀፅ 21

## በፍርድ ቤት የሚሰጥ ከአገር ማስወጣት ውሳኔ

- ጸኛው የውጭ ዜጋው በተፈረደበት ከዋናው ቅጣት ጋር የተያያዘ ተጨማሪ ቅጣት ለመጣል ከአገር እንዲወጣ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል። እንዲህ ዓይነቱ ከአገር የማስወጣት ወሳኔን መሰረዝ አይቻልም።
- የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀፅ 79

## በሸሸ/በተጸበቀ ሰራተኛ ላይ የሚቀርብ ክስ

- የውጭ ዜጎች የመኖሪያ ፈቃድ ህግ በሸሸ/በተጸበቀ ሰራተኛ ላይ የሚቀርብ ክስ ማለት የቤት ሰራተኛው ስለመጸበቁ ወይም ስለመጥፋቱ የሚያሳውቅና በስፖንሰሩ ሰራተኛው በጠፋ በአንድ ሳምንት ውስጥ ለአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚቀርብ ማመልከቻ ነው። ይህ ክስ አንዴ ከቀረበ፣ ስፖንሰሩ ክሱን ማንሳት ወይም ሂደቱን ማስቆም አይችልም። በሸሸ/በተጸበቀ ሰራተኛ ላይ የሚቀርብ ክስ ሰራተኛው በተያዘ ጊዜ ወዲያውኑ ከአገር የማስወጣት እርምጃ እንዲደርስበት ምክንያት ይሆናል። የቤት ሰራተኛው በስፖንሰሩ ላይ ክስ ወይም ቅሬታ አቅርቦ በቤት ሰራተኞች ክጥር አስተዳደር ክፍል ካስመዘገበ በኋላ ስፖንሰሩ በሸሸ/በተጸበቀ ሰራተኛ ላይ የሚቀርብ ክስ መመስረት አይችልም። ማመልከቻ ማስመዝገብ አይችልም ። ጉዳዩ ከምርመራ ወደ ቤት ውስጥ ሰራተኞች ቅጥር አስተዳደር የሚመራ ይሆናል።

የፖሊስ አባላት  አንድን ተጠርጣሪ ከምርመራ በፊት ከ 48 ሰዓት ያህል በእስር የማቆየት መብት አላቸው።

→

መርማሪው ተከሳሹ ቃሉን ከተቀበሉ በኋላ  በቁጥጥር ስር ከዋለበት ቀን ጀምሮ በቀላል ደንብ መተላለፍ የተጠረጠረ ከሆነ  ከ 10 ቀናት ለማይበልጥ ጊዜ በጊዜያዊነት እንዲታሰር ሊያዝ ይችላል ፤ በአንፃሩ በወንጀል ክስ ሲሆን  ከ 21 ቀናት እንዲታሰር ሊያዝ  ይችላል።

→

ተከሳሹ በ 48 ሰዓታት ውስጥ ፍርድ ቤት አማይቀርብ ከሆነ ለፍርድ ቤት በቁጥጥር ስር ለዋለበት ይግባኝ የማለት መብት አለው።

→

ፍርድ ቤቱ በተከሳሹ ላይ የቀረበውን ክስ ከሰማ በኋላ የእስር ቀናት የእስር ማራዘሚያ በአጠቃላይ ከ 30 ቀናት የእስር ማራዘሚያ ትዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

↓

የወንጀል ችሎቱ በተከሳሹ ላይ የቀረበውን ክስ ከሰማ በኋላ የ30 ቀናት የእስር ማራዘሚያ  ምጣኔ በአጠቃላይ ቢበዛ ከ 90 ቀናት የእስር ማራዘሚያ ትዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

* የፀጥታ ኃላፊዎች ወደ ሀገሩእንዲመለስ የተወሰነበትን ግለሰብ  ከ 30 ቀናት ላልበለጠ  ጊዜ አስሮ የማቆየት መብት አላቸው

## ለፖሊስ ጣቢያ የሚቀርቡ ክሶች

የወንጀል ወይም ቀላል የደንብ መተላለፍ አቤቱታ ሲቀርብ ጉዳዩ ድርጊቱ በተከሰተበት አካባቢ ለሚገኝ ፖሊስ መኮንን መቅረብ ያለበት ሲሆን፣ መኮንኑ አቤቱታን መመዝገብ አለበት። በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርአት ህግ አንቀጽ 40 መሰረት የፖሊስ መኮንኑ ክሱን አለመዘግብም የማለት መብት የለውም። የጣቢያው መኮንን አቤቱታውን አለመዘግብም ካለ የሚከተለውን ማድረግ ይችላሉ፡ -

የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር ክፍል ለሆነው የቁጥጥርና የኢንስፔክሽን ክፍል ክፍል ክስተቱን ማሳወቅ፣

→

አቤቱታውን በጽሑፍ ከነማብራሪያው ለጣቢያው ዋና ኃላፊ መስጠት።

→

የፖሊስ ጣቢያው ኃላፊ አለመዘግብ ካለ የጽሑፍ አቤቱታዎን ለአካባቢው የፖሊስ አዘዥ ማቅረብ ይችላሉ።

→

የአካባቢው የፖሊስ አዘዥ ክሱን አለመዘግብ ካለ ቅሬታውን በጽሑፍ ለአካባቢው ጸጥታ ዳይሬክተር ማስገባት ይችላሉ።

## ለምርመራ ክፍል የሚቀርቡ አቤቱታዎች

ጉዳዩ ቀላል የጸንብ መተላለፍ አቤቱታ ሲሆን፣ የመመርመር ስልጣን ያላቸው በአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር ያሉ መርማሪዎች ናቸው። መርማሪዎቹ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርአት ህግ አንቀጽ 40 መሰረት ክሱን ጉዳዩን አንመረምርም የማለት መብት የላቸውም። መርማሪዎቹ አቤቱታውን አንመረምርም ካሉ የሚከተለውን ማድረግ ይችላሉ፡ -

ክሱን ለምርመራ ክፍሉ ኃላፊ በጽሑፍ ማቅረብ፣ የፖሊስ ጣቢያው ኃላፊ አልመዘግብ ካለ የጽሑፍ አቤቱታዎን ለአካባቢው የፖሊስ አዛዥ ማቅረብ ይችላሉ።

→

ኃላፊው አስፈላጊ ሂደቶችን ለማሟላት ፈቃደኛ ካልሆነ፣ የጽሑፍ አቤቱታዎን ለክልሉ የምርመራ ዳይሬክተር ማቅረብ ይችላሉ።

↵

የአካባቢው የምርመራ ኃላፊ አስፈላጊ ሂደቶችን ለማሟላት ፈቃደኛ ካልሆነ፣ የጽሑፍ አቤቱታዎን ለአጠቃላይ የምርመራ ክፍለ ዳይሬክተር ጄኔራል ማቅረብ ይችላሉ።

## ለአቃቤ ሕግ የሚቀርቡ አቤቱታዎች

ጉዳዩ ከወንጀል ጋር ተዛማጅነት ካለው አቤቱታዎን በጽሁፍ በቀጥታ ለጠቅላይ አቃቤ ህግ ቢሮ ማቅረብ ይችላሉ። የአቤቱታው ይዘትም የወንጀል ድርጊቱ ስለተፈፀመበት ቀን እና ቦታ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ ዝርዝሮችን ማካተት አለበት። ጠቅላይ አቃቤ ህጉም በዚህ መሰረት የቀረበለትን አቤቱታ ለዚህ ጉዳይ ወደ ተሾመው መኮንን ያስተላልፋል።

# የሥራ አቤቱታ አቀራረብ ቅደምተከተል

ከቤት ሰራተኞች ቅጥር አስተዳደር ቅሬታ ማቅረብ፣

→

የሠራተኛውን መብት በማስጠበቅ ለማስታረቅና ስምምነት ላይ ለመድረስ መሞከር፣

→

ማስታረቅ ና ስምምነት ላይ መድረስ ካልተቻለ ጉዳዩን ወደ ያለ ክፍያ ሰራተኞች ፍርድ ቤት ይወሰዳሉ።

- ሰራተኛው በሰው ሃይል ባለሥልጣን ስር ወደላው የሰደተኛ ሰራተኞች መጠለያ ለመግባት የማመልከት መብት አለው፣
- የአመልካቹ እድሜው ቢያንስ 20 ዓመት  መሆን አለበት፣
- አመልካቹ በወንጀል ጉዳይ የሚፈለግ ከሆነ ወይም በህግ አስፈጻሚ ባለስልጣናት ተፈላጊ ከሆነ ማመልከቻው ውድቅ ይሆናል፣
- ወደ መጠለያው ውስጥ የሚገባ ሰው የምግብ፣ የመጠጥ፣የመኖሪያ ቤት እና የሥነ ልቦና ብሎም ማህበራዊ ክብካቤ ይደረግለታል፣
- እያንዳንዱ ተጠላይ ሰብዓዊ ክብሩ ብሎም ለሥነ - ልቦና ወይም ለሞራል ጉዳት ያለመጋለጥ መብቱ የተጠበቀ ነው፣
- እያንዳንዱ ተጠላይ በመጠለያው  ደንብና እና ስርዓቶች መሰረት ፍላጎቶቹን የማሟላት መብት አለው፣
- ለራሱ ጥቅም ሲባል በጥቂት አጋጣሚዎች ካልሆነ በስተቀር ተጠላይ የጉብኝት መብቱ የተጠበቀ ነው ፣
- ተጠላይ ቅሬታውን በልዩ ባለሙያዎቹ ወይም በማዕከሉ ዳይሬክተር በኩል  የማቅረብ መብት አለው፣
- ተጠላይ ማእከሉን በፈቃደኝነት የመተው መብት አለው፣
- ተጠላይ ሁኔታው ከተቀየረ ከማዕከሉ ወጥቶ ወደ ወኪሉ የመመለስ ወይም ሀገሩን ለቆ መሄድ ይችላል፣
- የህግ አስፈጻሚ አካላት ሲጠይቁ  ህጋዊ በሆነ መልኩ ተጠላይ በቁጥጥር ስር ውሎ እንዲሰጥ ይደረጋል።

| የመኖርያ ፈቃድ ቁጥር | የመኖርያ ፈቃድ ዓይነት |
|---|---|
| አንቀፅ 14 | የጊዜያዊ መኖሪያ ፈቃድ የሚቆየው ለ 3 ወራት ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በሀገሪቷ ፍላጎት ወይም ለህክምና ለሚወስዱ ወይም በመንግስት ስልጠና ለሚወስዱና ለስብሰባ ለሚገቡ ግለሰቦች የስደተኞች ቢሮ አስተዳደር በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት ፍቃዱ እስከ አንድ ዓመት ሊራዘም ይችላል |
| አንቀፅ 17 | የሲቪል /የመንግስት የመኖርያ ፈቃድ |
| አንቀፅ 18 | የግሉ ዘርፍ የመኖርያ ፈቃድ |
| አንቀፅ 19 | ለቢዝነስ ወይም ለኢንዱስትሪ ወይም በሙያ ስራዎች ለሚሰማሩ የሚሰጥ የመኖርያ ፈቃድ |
| አንቀፅ 20 | የቤት ሰራተኛ የመኖርያ ፈቃድ |
| አንቀፅ 22 | የቤተሰብ ጥገኛ የመኖርያ ፈቃድ |
| አንቀፅ 23 | የትምህርት መኖሪያ ፈቃድ |
| አንቀፅ 24 | ያለስራ ላሉና በቆይታቸው የገቢ ምንጭ ማቅረብ ለሚችሉ የሚሰጥ የመኖርያ ፈቃድ (ወኪሉ እራሱ ) |

| ተቋም | አድራሻ | ስልክ |
| --- | --- | --- |
| የቤት ሰራተኞች አስተዳደር | ሩማቲያ - ብሎክ 7 - የመንገድ ቁጥር 78 - ከሀሰን አል በና መንገድ የሚገነጠል - ከ ሩማቲያ ሙኽታሪያ አጠገብ። | xxxxxxxx |
| የወንጆች ከአገር ማስወጫ ጣያ | ጀሊብ አል ሽዩህ፣ ብሎክ 1፣ ካሊድ ኢቃብ አል አሽሀብ መንገድ፣ ከአል ጋዛሊ መንገድ ፊት ለፊት | 24336942 |
| የፍትህ ህንጻ፣ የሰራተኞች ፍርድ ቤት | ዌት ሲቲ፣ አሊ አል ሳሊም መንገድ፣ ከከታማ ማዘጋጃ ጋርደን ፊት ለፊት | 1881100 |
| የፍተሻና ኢንስፔክሽን ክፍል | ሻርቅ ብሎክ 1፣ የመንገድ ቁጥር 104 ከወርባ ባንክ ፊት ለፊት | 1888888 |
| የስደተኛ ሰራተኞች መጠለያ ጣቢያ ማእከል | ጀሊብ አል ሽዩህ ፣ ብሎክ 2፣ የመንገድ ቁጥር 139 | xxxxxxxx |
| ድንገተኛ/የአደጋ ጊዜ | | 112 |

| ኤምባሲ | አድራሻ | ስልክ | ድህረ ገፅ እና/ወይም ኢሜል |
|---|---|---|---|
| ህንድ | አል ደአያህ፣ ድፕሎማቲክ ኤበርሁድ፣ አረቢያን ገልፍ መንገድ | 22530600<br>22530612<br>22530614 | www.indembkwt.org |
| አንዶኔዥያ | አል ደአያህ፣ ብሎክ 1፣ አህማዲ አል ሩሚ መንገድ፣ ቪላ ቁጥር 12 | 22531025 | www.kuwaitcity.kemlu.go.id<br>kuwait.kbri@kemlu.go.id |
| ስሪላንካ | ጃብሪያ ብሎክ 10፣ መንገድ 107፣ የቪላ ቁጥር 1 | 25354633 | www.slembkwt.org/contact-us-main-menu-43<br>lankemb@qualitynet.net |
| ኢትዮጵያ | ጃብሪያ፣ ብሎክ 10፣ መንገድ 107፣ ቪላ ቁጥር 30 | 25330128 | emailethiokuwait@yahoo.com<br>ethiokwt@qualitynet.net |

| ኤምባሲ | አድራሻ | ስልክ | ድህረ ገፅ እና/ወይም ኢሜል |
|---|---|---|---|
| ፊሊፒን | አል ሲዲቅ፣ ብሎክ 1፣ መንገድ 101፣ ቪላ ቁጥር 816 | 22022166 | http://www.kuwaitpe.dfa.gov.ph |
| ኔፓል | ጃብሪያ፣ ብሎክ 8፣ መንገድ 13፣ ቪላ ቁጥር 514 | 25321603 | info@nepembku.org |
| ባንግላዴሽ | ካልድያ፣ ብሎክ 2፣ መንገድ 29 ቪላ ቁጥር 11 | 24913219 | www.bdembassykuwait.org<br>info@yourdomail.com<br>bbood@kms.net<br>mission.kuwait@mofa.gov.bd |
| ኤርትራ | ጃብሪያ ብሎክ 9፣ መንገድ 21 ፣ ቪላ ቁጥር 9 | 25317426 | |

| ኤምባሲ | አድራሻ | ስልክ | ድህረ ገፅ እና/ወይም ኢሜል |
|---|---|---|---|
| ቶጎ | በያን፣ ብሎክ 4፣ መንገድ5፣ ቪላ ቁጥር 17 | 25379261 | www.ambatogokuwait.com<br>ambassatokoweit@hotmail.com |
| ሴራሊዮን | አልዘህራ፣ ብሎክ 8፣ መንገድ 800፣ ቪላ ቁጥር 169 | 25243246 | info@salembassy-kw.org |
| ዚምባቡዌ | ሰልዋ፣ ብሎክ 9 ፣ መንገድ 6 ፣ ቪላ ቁጥር 8 | 25620845 | zimtripoli@yahoo.co.uk<br>zimkuwait2010@hotmail.com |
| ኬንያ | አል ዘህራ፣ ብሎክ 8 መንገድ 807 ፣ ቪላ ቁጥር 133 | 25243771 | kenemb.kuwait@gmail.com<br>kuwait@mfa.go.ke |

| ኤምባሲ | አድራሻ | ስልክ | ድህረ ገፅ እና/ወይም ኢሜል |
|---|---|---|---|
| ቤኒን | አል ጸአያ ፣ ብሎክ 2 ፣ አል አስቲቅላል መንገድ ፣ ቤት ቁጥር 8 ቢ | 25242560 | ambeninkwt@hotmail.com |
| ናይጄሪያ | ምአራብ ሙሽሪፍ ፣ ብሎክ 1፣ መንገድ 103 ፣ ቪላ ቁጥር 8 | 25379540<br>25379541 | embassyofnigeriakuwait.com<br>nigeriankuwait@yahoo.co.uk |
| ሴኔጋል | ረውዳ፣ ብሎክ 3፣ መንገድ 35 ፣ የቤት ቁጥር 9 | 22510823 | Embassysenegalese721@yahoo.com |
| ማላዊ | አልሹሀዳ ፣ ብሎክ 5፣ መንገድ 512 ፣ ቤት ቁጥር 3 | 25235416<br>25235419 | info@malawiembkuwait.com<br>malawikuwait@gmail.com |

| ኤምባሲ | ሀገር | ስልክ | ጽሁፈ ገፅ እና ኢሜል |
|---|---|---|---|
| ማዳጋስካር | ሪያድ | +966 567351840<br>+966 507882927<br>+966 544580298 | vierra74@yahoo.fr |
| ማሊ | ሪያድ | +966 567215202<br>+966 530661160<br>+966 590005240<br>+966 556706658 | zarho2005@hotmail.com |
| ጋምቢያ | ሪያድ | +966 14659996 | |
| ጋና | ሪያድ | +966 114545126 | |

| ኤምባሲ | ሀገር | ስልክ | ፖስታ ሳጥን እና ኢሜል |
|---|---|---|---|
| ናሚቢያ | ካይሮ | +202 23584467<br>+202 2378663<br>+202 2378664 | |
| ታንዛንያ | ሪያድ | +966 14542833<br>+966 12051541 | |
| ካሜሮን | ሪያድ | +966 14880022<br>+966 14880203 | |
| ኮትዲቯር | ሪያድ | +966 114708387 | |

| ተቋም | አድራሻ |
| --- | --- |
| የሕዝብ ምርማራ ክፍል | ሳልምያ፣ ሀመድ አል ሙባረክ መንገድ፣ ብሎክ 5፣ መንገድ 104 ፣ ከቦሌፉርድ ፊት ለፊት |
| የአል አሲማህ የምርመራ ክፍል | ሻርቅ፣ ብሎክ 4፣ አህመድ አልጀቢር መንገድ፣ ከድስማንአ ደባባይ አጠገብ፣ |
| የሀዋሊ የምርመራ ክፍል | ሀዋሊ ፣ ብሎክ 9፣ መንገድ ቁጥር 247፣ ከሸርሃቢል መንገድ የሚገነጠለው፣ |
| የሙባረክ አል ከቢር የምርመራ ክፍል | ሰባህ አል ሳሊም የህግ ማስከበር ዳይሬክቶሬት፣ ሰባህ አሳሊም ህብረት ስራ ማህበር አጠገብ |
| የአልፈርዋንያ የምርመራ ክፍል | አል ራብያ የህግ ማስከበር ዳይሬክቶሬት፣ አል ራብያ ህብርት ስራ ማህበር አጠገብ |
| የአል አህመዲ ዞን የምርመራ አስተዳደር | የአል አህመዲ _ሙስጠፉ ከረም ማዞሪያ_የአል አህመዲ ፖሊስ ጣቢያ |
| የአል ጀህራ የምርመራ ክፍል | ደቡብ ጀህራ፣ _ሰአድ አል አብደላ አካባቢ ፣ የድሮ ደቡብ አል ጀህራ ፖሊስ ጣቢያ |
| ልዩ የምርመራ ክፍል | አሳልሚያ ፣ የሕዝብ ምርማራ ክፍል ህንጻ |

| ተቋም | አድራሻ | የስልክ ቁጥሮች |
|---|---|---|
| አቃቢ ህግ | ኩዌት ሲቲ፣ የፍትህ ፓላስ | xxxxxxxx |
| የአል አህመዲ አቃቢ ህግ | ደቡብ ሱባህያ፣ የአል አህመዲ ፍርድ ቤቶች ህንጻ | 1883300 |
| የአል ጀህራ አቃቢ ህግ | አል ጀህራ፣ ከሳሊም አል አሊ የመዝናኛ አዳራሽ በስተ ጀርባ ፣ ከስደተኞች አስተዳደር አጠገብ | 24584328 |
| የአል አሲማ አቃቢ ህግ | የፍትህ ፓላስ፣ 8ኛ ፎቅ | xxxxxxxx |
| የሀዋሊ አቃቢ ህግ | ሀዋሊ አደባባይ፣ ብሎክ 11፣ አል ረቢአ መንገድ 1 ፣ ህንፃ 15 ፣ ከወ ኢንጂነሪንግ እና ከሀዋሊ ትራፊክ አስተዳደር አጠገብ | 25667016 |
| የአልፈርዋንያ አቃቢ ህግ | አል ረቀኢ፣ ፍርድ ቤቶች ህንጻ | xxxxxxxx |

## የአሲማህ አስተዳደር ክልል

| የፖሊስ ጣቢያው ስም | የሚሸፍናቸው አካባቢዎች | የስልክ ቁጥሮች |
|---|---|---|
| አል የርሙክ | አል የርሙክ | 25323519 |
| አል ሻሚያ | አሻሚያ፣ አሸዌህ መኖሪያ ሰፈር | 24845953<br>24827178 |
| ከይፋን | ከይፋን፣ አል ኻሊዲያ | 24832839 |
| አሸዌህ የኢንዱስትሪ አካባቢ | አሸዌህ የኢንዱስትሪ አካባቢ፣<br>የአልሳባህ ሜዲካል አካባቢ | 24813726 |
| አልኻሊድያ | አልኻሊድያ | 24826141<br>24826144 |
| አሱለይቢኻት | አሱለይቢኻት፣ ደሃ፣ ገርናደ፣<br>ሰሜን - ምዕራብ አሱለይቢኻት፣<br>የደሃ መዝናኛዎች<br>ገርናጣ | 24870716<br>24861782 |
| የ ፊልካ ሴት | የ ፊልካ ደሴት | 66766638 |
| አሱራ | አሱራ<br>ቀርጡባ | 25312220 |
| አብዱሏህ  አል ሳሊም | አብደላ አሳሊም<br>አኑዝሀ | 22570000<br>22544160 |

## የአሲማህ አስተዳደር ክልል

| የፖሊስ ጣቢያው ስም | የሚሸፍናቸው አካባቢዎች | የስልክ ቁጥሮች |
|---|---|---|
| አል ፈይሀ | አል ፈይሀ፣ አል ነዝሃ | 22547168<br>22547142 |
| አል ደስማ | አል ደስማ፣<br>በኒድ አልጋር | 22531914<br>22531917 |
| አልቃዲስያ | አልቃዲስያ፣<br>አመንሱርያ | 22574386<br>22575665 |
| አል ረውዳ | አል ረውዳ | 22546257<br>22573031 |
| አል ደእያ | አል ደእያ፣ የኤምባሲዎች አካባቢ | 22571081 |
| አሷሊህያ | አሷሊህያ | 22427157<br>22422353 |
| አልአዳይልያ | አልአዳይልያ | 22562197<br>22541216 |
| ሸርቅ | ሸርቅ፣<br>አል ሰዋቢር፣<br>ደስማን፣ ገልፍ መንገድ (ከታላቁ መስጊድ እስከ ኩዌት ታወርስ) | 22424019 |

## የጃህራ አስተዳደር ክልል

| የፖሊስ የጣቢያው ስም | የሚሸፍናቸው አካባቢዎች | የስልክ ቁጥሮች |
|---|---|---|
| አልቀሸናኢያ | አልቀሸናኢያ፣<br>ከባሪ አል አዋዝም | xxxxxxxx |
| አልጀህራ | አልጀህራ፣ ተፈጥሯዊ ክልል፣<br>ተፈጥዊ ክልል መንገድ<br>አልመህምያት<br>ጠሪቅ አልመህምያት | 24551466 |
| አል ዋሃ | አዋሃ፣ የፈረስ መጠለያ፣<br>አል ሳሊሚ (እስከ ወታደራዊ<br>ካምፕ) | 24557748 |
| አል ነኢም | አል ነኢም፣<br>አል ቀስር | 24564472 |

| የፖሊስ የጣቢያው ስም | የሚሸፍናቸው አካባቢዎች | የስልክ ቁጥሮች |
|---|---|---|
| አል ጃበር አል አህመድ | አል ጃበር አል አህመድ | 96655598 |
| አሱለይቢያ | አሱለይቢያ፣ አሱለይቢያ<br>ኢንዱስትሪያል፣ ከከፊል 4ኛው<br>የቀለበት መንገድ  እስከ ከበድ<br>አካባቢ | 24678344 |
| ከበድ | ከበድ | 25370417 |
| አል ሰብያህ | አል ሰብያህ | 24562074 |
| አል ሙጥላአ | አል ሙጥላአ | 24575712 |

## የጀህራ አስተዳደር ክልል

| የፖሊስ የጣቢያው ስም | የሚሸፍናቸው አካባቢዎች | የስልክ ቁጥሮች |
|---|---|---|
| አል ቀይረዋን | አል ቀይረዋን፣<br>አል ነህዳ | 24661732 |
| ሰአድ አል አብደላ | ሰአድ አል አብደላ | 24538126 |

| የፖሊስ የጣቢያው ስም | የሚሸፍናቸው አካባቢዎች | የስልክ ቁጥሮች |
|---|---|---|
| ተይማ | ተይማ፣<br>አል ጀህራ ኢንዱስትሪያል፣<br>አል ናሲም፣<br>አል ኡዩን፣ አል ሳልሚ (እስከ ኪሎ 41) | 24573958 |

## የሙባረክ አል ከቢር አስተዳደር ክልል

| የፖሊስ የጣቢያው ስም | አካባቢው | የስልክ ቁጥሮች |
|---|---|---|
| የአል አዳን ፖሊስ ጣቢያ | አልአዳን፣ አል መሲላህ፣ አልመሳይል፣ አል ቁሱር፣ አል ጆመይሪያህ፣ አልፊኒጢስ | 25421337 |
| አቡ ፈጢራህ | አቡ ፈጢራህ፣ አቡ አልሃሳኒ | xxxxxxxx |
| ሰባህ አል ሳሊም | ሰባህ አል ሳሊም፣ ሱብሃን | 25514800 |
| ሙባረክ አል ከቢር | ሙባረክ አል ከቢር፣ አል ቀሪን፣ አል ቀሪን ሱቅ | 25438063 |

## የአል ፈርዋንያ አስተዳደር ክልል

| የፖሊስ ጣቢያው ስም | አካባቢው | የስልክ ቁጥሮች |
|---|---|---|
| ክይጣን | ክይጣን | 24722590 |
| አል አምርያ | አል አምርያ | 24742662 |
| አል ፈርዋንያ | አል ፈርዋንያ | 24711977 |
| አል አንደሎስ | አል አንደሎስ፣<br>አል ሩቀኢ፣<br>አል ረይ | 24898062 |
| አል ራብያ | አል ራብያ | 24742160 |
| አል አሪደህያ | አል አሪደህያ | 24881273 |
| ሰባህ አል ናስር | ሰባህ አል ናስር | 24898754<br>24898751 |
| አል ረሃብ | አሪሃብ | 24310574<br>24318390 |
| ኡብደላ አል ሙባረክ | ኡብደላ አል ሙባረክ | 24363047<br>24363057 |
| ጁለይብ አል ሸዩኽ | ጁለይብ አል ሸዩኽ<br>አልደጂጅ፣<br>ኤርፖርት፣<br>ሰብሀን | 24311234<br>24311335 |

## የአል ፈርዋንያ አስተዳደር ክልል

| የፖሊስ ጣቢያው ስም | አካባቢው | የስልክ ቁጥሮች | የፖሊስ ጣቢያው ስም | አካባቢው | የስልክ ቁጥሮች |
|---|---|---|---|---|---|
| ኢሽቢሊያ | ኢሽቢሊያ | 24389661 | አል ፎርደውስ | አል ፎርደውስ | 24893091 |

## የሐዋሊ አስተዳደር ክልል

| የጣቢያው ስም | አካባቢው | የስልክ ቁጥሮች |
|---|---|---|
| መይዳን ሀውሊ | መይዳን ሀዋሊ፣<br>አል ሸዕብ አልበህሪ፣<br>አል ሸዕብ መኖሪያ መንደር | 25626971<br>25629910 |
| አል ጃብርያ | አልጃቢርያ | 25315393<br>25312559 |
| ሰልዋ | ሰልዋ፣<br>አልብደአ | 25624496<br>25626565 |
| አል ሳልምያ | አል ሳልምያ | 25713218<br>25727806 |

## የአሕመዲ አስተዳደር ክልል

| የጣቢያው ስም | አካባቢው | የስልክ ቁጥሮች | የጣቢያው ስም | አካባቢው | የስልክ ቁጥሮች |
|---|---|---|---|---|---|
| ጃበር አል አሊ | ጃበር አል አሊ | 23842492<br>23842493 | አል ኑወይሲብ | አል ኑወይሲብ | 23950975<br>23950607 |
| ፋሀድ አል አህመድ | ፋሀድ አል አህመድ | 23630984<br>23630978 | አልፎሀይሒል | አልፎሀይሒል | 23910014<br>23912959 |
| አል ወፍራ | አል ወፍራ | 23810411 | ሚናእ አብዱሏህ | ሚናእ አብዱሏህ | 23261983<br>23261145 |
| አቡ ሁለይፋ | አቡ ሁለይፋ | 23714753<br>23722151 | አሊ ሰባህ አል ሳሊም | አሊ ሰባህ አል ሳሊም | 23280383<br>23280277 |
| አል ሸባህያ | አል ሸባህያ | 23618557 | | | |

# የአሕመዲ አስተዳደር ክልል

| የጣቢያው ስም | አካባቢው | የስልክ ቁጥሮች | የጣቢያው ስም | አካባቢው | የስልክ ቁጥሮች |
|---|---|---|---|---|---|
| አል ሪቃ | አል ሪቃ፣ አል ኡጋኢ | 23940700 | አል ፊንጣስ | አልፊንጣስ፣<br>አል መሀቡላ | 23903744<br>23903606 |
| ሀድያ | ሀድያ | 23960513 | አል ጣዒር | አል ጣዒር | 23830500<br>23840900 |
| ሹዓይባ ኢንዱስትሪያል | ሹዓይባ ኢንዱስትሪያል | xxxxxxxx | አል አህመዲ | አል አህመዲ | 23980401<br>23980304 |
| አል ዞር | አል ዞር | 23950160 | ሰባህ አል አህመድ | ሰባህ አል አህመድ | xxxxxxxx |

## የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚንስቴር

የመኖሪያ ፈቃድንና የፈቃዱን ማብቂያ በተመለከተ፡

www.e.gov.kw/sites/kgoEnglish/Pages/eServices/MOI/ResidencyExpiry.aspx

የጉዞ ክልከላን በተመለከተ፡

www.e.gov.kw/sites/kgoEnglish/Pages/eServices/MOJ/BanTravel.aspx

## የፍትህ ሚኒስቴር

የጉዳዩ ኢሌክትሮኖክ ቁጥር፣ በፖኪስ ጣቢያ የጉዳዩ ቁጥር፣ በአቃቤ ህግ የጉዳዩ ቁጥር ፣ በፍርድ ቤት የጉዳዩ ቁጥር
የጉዳዩ የአፈጻጸም መዝገብ ቁጥር፡

https://www.kuwaitcourts.gov.kw/searchPages/searchCases.jsp

ለእስራት፣ ጉዞ ክልከላ፣ በራስዎ ላይ የተከፈተ ፋይል፣ በግለሰብ ላይ የተከፈተ ፋይል፡

https://www.kuwaitcourts.gov.kw/searchPages/searchCivil.jsp

1 —

ህግ ቁጥር 68/2015፣ የቤት ሰራተኞች ጉዳይን በተመለከተ

2 —

የወንጀለኛ መቅጫ ህግ 16/1960

3 —

በ17/1960 የወጣው የወንጀል መቅጫና የአፈፃፀም ህግ ቁጥር 17/ 1960

4 —

በ91/2013 የወጣው ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር የሰዎች ንግድ መከላከል ህግ (ቁጥር 91 የ2013)

5 —

የቤት ሰራተኞች ጉዳይ ህግ ማስፈፀሚያ ደንብ ቁጥር 68/2015

6 —

በ 17/1959 የወጣው የአሚር የውጭ ዜጎች መኖርያ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 17/

* ይህ ህግና መመሪያ እ.ኤ.አ በህዳር 2018 የታተመ ነው።

* በዚህ መመሪያ ላይ የተጠቀሱት ፖሊሲዎችና ህግች ከላይ ከተጠቀሰው ቀን በኋላ ሊለወጡ ይችላሉ።

* በዚህ መመሪያ ላይ የተጠቀሱትአድራሻዎችና ስልክ ቁጥሮች ሊለወጡ ይችላሉ።

## የከፍተኛ ደረጃ ስፖንሰር

zain

Alghanim INDUSTRIES

## የፕላቲኒየም ደረጃ ስፖንሰር

## የወርቅ ደረጃ ስፖንሰር

شركة الغانم انترناشيونال للتجارة العامة والمقاولات ذ.م.م

Alghanim International General Trading & Contracting Co. W.L.L.

تمدين TAMDEEN GROUP

## ልዩ ምስጋና

GRID

MIGRANT-RIGHTS.ORG

## ይህ ህግና መመሪያ በሚከተሉት ቋንቋዎች ይገኛል፡

العربية / Arabic / العربية

الأنجليزية / English / English

الفرنسية / Le Français / French

الفلبينية - التغلوغ / Tagalog / Filipino

النيبالية / नेपाली भाषा / Nepalese

الأندونيسية / bahasa Indonesia / Indonesian

البنغالية / বাংলা ভাষা / Bengali

السنهالية - سريلانكا / සිංහල අක්ෂර මාලාව / Sinhalese

تيلوغو - الهند / తెలుగు / Telugu

المالیالامية - الهند / മലയാളം / India - Malyalam

الهندية / हिन्दी / India - Hindi

التاميل - الهند / தமிழ் / India - Tamil

أوردو - الهند / India - Urdu / اُردُو

مدغشقر / malagasy / Malagasi

الأمهرية - أثيوبيا / አማርኛ / Ethiopia - Amharic

OneRoofKW | 2537 5031 | 2573 5032 | info@oneroofkw.org | www.oneroofkw.org | 6036 7261